# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 154 ሚያዝያ 20 2003 ገጽ 1

**መከፋፈል በቃ!**

**በንድፈ ሃሳብ ደረጃ የመተባበርን አስፈላጊነትና ጠቀሜታን ማንም አይስተውም። ስለትብብር በየቦታው ሲሰበክ እንሰማለን። ችግሩ ያለው ከንግግር ባለፈ በተግባር መተባበር መቻል ላይ ነው። በተለይም በፓለቲካ ድርጅቶች መካከል ዘላቂና ፍሬዓማ የሆነ ትብብር መፍጠር ትዕግሥትና ጥበብን የሚጠይቅ ተግባር ነው።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ህወሃት በራሱ እና በአምሳሉ በፈጠራቸው ፓርቲዎች ውስጥ ሙስና በከፍተኛ ደረጃ መስፋፋቱን አመነ

የዘረኛውና አምባገነኑ አገዛዝ ኢህአዴግ ጥምር ፓርቲዎች ውስጥ የተስንሰራፋው ሙስና ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን ፓርቲው አደረኩት ባለው ጥናት ማረጋገጡንና ለመካከለኛ ደረጃ አባላቱ ገለጸ ማድረጉን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘገበ::

እንደ ኢሳት ዘገባ ሰሞኑን ከየክልሎቹ የተሰባሰቡ የወያኔ ኢህአዴግ ፓርቲና አጋሮቹ የመካከለኛ ደረጃ ኃላፊዎች በአዲስ አበባ የምክክር ስብሰባ ማድረጋቸው በዚሁም ስብሰባቸው ሙስና የፓርቲውን ህልውና የሚፈታተንበት ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ተደረገ የተባለው ጥናት ማጋለጡ ታውቁአል::

በኢህአዴግ ጥምር ፓርቲዎች ውስጥ ከፍተኛ የሙስና ምንጭ ሆነዋል ተብለው በጥናቱ የተጠቀሱት ሦስት አበይት ተቋማት እንደሆኑ የዜና ምንጮቹን በመጥቀስ የዘገበው ኢሳት፤ እነኝህ ተቋማት የመሬት አስተዳደር ጉዳይ፣ ገቢዎችና ጉምሩክ እና በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚሰሩ የፌዴራል መንግሥታዊ ተቋማትና ክልላዊ ተቋማት ናቸው በሚል በዝርዝር ማስቀመጣቸውን ገልጹአል::

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ግንቦት7 በአትላንታ የጠራው ህዝባዊ ስብሰባ በታላቅ ስኬት መጠናቀቁ ታወቀ

በሰሜን አሜሪካ የአትላንታ ግንቦት 7 ኮሚቴ ባዘጋጀው ህዝባዊ ስብሰባ ላይ ቁጥሩ ከፍተኛ የሆነ የአትላንታና አካባቢዋ ኢትዮጵያዊያን መገኘታቸውን ሪፖርተራችን ከስፍራው ከላከልን ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል።

የግንቦት 7 ሊ|መንበር ዶ|ር ብርሃኑ ነጋ እና በአትላንታ የኦነግ እንዲሁም የኦጋዴን ነጻነት ግንባር ተወካዮች በጋራ በተገኙበት በዚህ ህዝባዊ ስብሰባ ላይ ፡ ሶስቱም ድርጅቶች የወያኔ አገዛዝ በህዝባችን እና በአራችን ላይ እያደረሰ ያለውን በደልና ሰቆቃ ለማስቆም ሁሉም ኢትዮጵያዊ እጅ ለእጅ ተያይዞ በጋራ መታገል እንዳለበት ጥሪ አቅርበዋል።

በስብሰባው ላይ የመጀመሪያውን ንግግር ያደረጉት የኦጋዴን ነጻነት ግንባር የአትላንታ ተወካይ ፤ የወያኔ አገዛዝ በኦጋዴን ህዝባችን ላይ እየፈጸመ ያለውን የዘር ማጥፋት ወንጀል ለማስቆም በጋራ ከታገልን እና ኢትዮጵያ አገራችን ውስጥ ፍትህ ፤ እኩልነትና ነጻነት የሚረጋገጥበት ሥርዓት በጋራ መመሥረት ከቻልን ለኦጋዴን ህዝብ ከኢትዮጲያዊያን ወንድሞቹና እህቶቹ ጋር በአንድነት ከመኖር የተሻለ አማራጭ የለም በማለት የድርጅታቸውን አቋም አስታውቀዋል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የወያኔ አገዛዝ የስቴት ዲፓርትመንት በቅርቡ ያወጣውን የሰብ አዊ መብት ሪፖርት ርባና የለሽ ነው በማለት አጣጣለው

የአመሪካ መንግስት የስቴት ዲፓርትመንት በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚካሄደው የሰብዓዊ መብት ጥሰት አስመልክቶ በቅርቡ ያወጣውን አመታዊ ሪፖርት በተመለከተ የወያኔ ሹሞች በተለመደው ቅጥፈት ሪፖርቱ የተቃዋዎች አቤቱታ ላይ የተመሰረተና ያልተጣራ ፍሬ ቢስ ነው በማለት ማጣጣላቸውን ቮይስ ኦፍ አሜሪካ አስታወቀ።

በኢትዮጵያ የሚገኘውን የሰባዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታ በሚመለከት የዘረኛውን አገዛዝ ያደናገጠና ያበሳጨ ሪፖርት አወጣ ሲሆን በሪፖርቱ ላይ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ከፍተኛ ገንዘብ ወጪ በማድረግ የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ እንቅስቃሴ የመቆጣጠር ስራ እየሰራ መሆኑን፣ ለዚህም ስራ የግለሰቦችን የእለት ከእለት እንቅስቃሴ በመከታተል ሪፖርት የሚያቀርቡ ቅጥረኞች እንዳሉት ማጋለጡ ይታወሳል::

ባለ 56 ገጽ የዘንድሮው የስተት ዲፓርተመንት ሪፖርት ዘረኛውና አፋኙ የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያ ውስጥ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽና የመጻፍ መብቶች እጂግ የገደበ መሆኑን ፣ ጋዜጠኞችን የማዋከብ የማሰርና የማንገላታት ተግባር የተስፋፋ መሆኑን፣ ከውጭ ሃገራት ወደ ኢትዮጵያ የሚተላለፉ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ስርጪቶች መታፈናቸውን፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምንም አይነት የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንዳይኖር እገዳ መጣሉን፣ እንዲሁም በሃገሪቱ በርካታ የሆኑ መረጃዎች የሚገኙባቸው የኢንተርኔት ላይ የመረጃ ድረገጾች የተዘጉ መሆናቸውን በዝርዝር በመጥቀስ ማጋለጡ ይታወቃል:: ከዚህም በተጨማሪ ሪፖርቱ በኢትዮጵያ የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲ ትልቅ ጥያቄ ውስጥ የገባ መሆኑን፣ ሃገሪቱ እየተመራች ያለቺው በአንድ አምባገነናዊ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የሐረር ዞን የመሬት አስተዳደርና የካሳ ክፊያ ሹም አገዳደልን አስመልክቶ በግንቦት 7 ድምጽ የተዘገበው ዜና እርምት እንዲደረግበት የሃራሪ ሪቫይቫል ንቅናቄ በመባል የሚታወቅ ድርጅት ጠየቀ

የሃራሪ ሪቫይቫል ሙቭመንት በመባል የሚታወቅ ድርጅት ሚያዚያ 16 ቀን 2003 ዓም ለንቅናቄያችን የህዝብ ግንኙነት በጻፈው ደብዳቤ የሃራሪ ክልል የመሬት አስተዳደርና የካሳ ክፍያ ሹም የነበሩት ሟቹ አቶ ሐሽም እንዲሪስ የተገደሉት ክልሉን በጋራ በሚያስተዳድሩት ሁለቱ የወያኔ |ኢሃደግ ድርጅቶች የተቀነባበረ ሴራ መሆኑን አጋልጦ ሚያዚያ 11 ቀን 2003 በግንቦት 7 ድምጽ የቀረበው ዘጋባ እርምት እንዲደረግበት ጠየቀ።

አቶ ሐሽም እንዲሪስ በህይወት ዘመናቸው ሙሉ ስራ ላይ በነበሩበት ወቅት ህዝባቸውን በታማኝነት ያገለገሉ እንደነበሩና በዚህም ስነምግባራቸው ምክንያት በአካባቢው ህብረተሰብ ዘንድ የተወደዱ እና የተከበሩ ነበር ያለው የሃራሪ ሪቫይቫል ንቅናቄ ደብዳቤ ፤ ግለሰቡ በወያኔ ሥርዓት ላይ ባላቸው ተቃውሞ ምክንያት በቅርቡ ተደርጎ በነበረው የምርጫ ድራማ በርሳቸው ይመራ የነበረው የሃራሪ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ በክልሉ ምርጫ ላይ እንዳይሳተፍ ሆን ተብሎ ማዋከብ እና ማስፈራራት እንደደረሰበት በዚህም ምክንያት ምርጫውን ትቶ ለመውጣት እንደተገደደ ገልጿል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## አፋኙ ወያኔ የህዝብን ቁጣ መገደብ አልቻለም፣ በምሥራቅ ወለጋ በባኮ አዲስ ህዝባዊ አመጽ ተቀሰቀሰ

በቱኒዚያ ተቀስቅሶ በበርካታ የሰሜንና የመካከለኛው አፍሪቃ ሃገራት እየተቀጣጠለ ያለው ህዝባዊ አመጽ የአፍሪቃ ቀንድንም ማጋል የጀመረ ሲሆን ካለፈው ወር ጀምሮ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች እየተቀሰቀሰ ያለው ህዝባዊ አመጽ አሁንም በመቀጠል በባኮ ከተማ የሚገኙ ተማሪዎች ህዝባዊ አመጽ መጀመራቸውን ዘጋቢያችን ከስፍራው ያስተላለፈልን ሪፖርት አመለከተ:: ህዝባዊ አመጹን የቀሰቀሱት በባኮ ከተማ የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች መሆናቸውም የደረሰን ዜና አመልክቷል።

በተማሪዎች የተቀሰቀሰውን ህዝባዊ አመጽ ለማፈን ከየት እንደመጡ ሳይታወቅ እጂግ በርካታ የፌደራል ፖሊሶች ከተማዋን ማጥለቅለቃቸውንና በከፍተኛ ጭካኔ አመጹን ያስነሱትን ተማሪዎች ሲደበድቡም መታየታቸውን የአይን እማኞችን በመጥቀስ ዘጋቢያችን በላከልን ሪፖርት ገልጿል::

እንደሪፖርተራችን ዘገባ በባኮ ከተማ አመጹ ከተጀመረ አንድ ሳምንት የሚሆን ጊዜ ማስቆጠሩን፣ በከተማዋም ከፍተኛ የተኩስ ልውውጥ መደረጉንና፣ በአመጹ ተሳትፋቺኋል የተባሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎች ታፍሰው ወደአልታወቀ ቦታ ተወስደው መታሰራቸውን ተያይዞ የደረሰን ዜና አመልክቷል::

ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው አንዳንድ የከተማዋ ነዋሪዎች እንደገለጹት ተማሪዎቹ አመጹን ሊያነሳሱ የቻሉበት ዋና ምክንያት የኑሮ ውድነት ቢሆንም ባጠቃላይ የወያኔ አገዛዝ በህዝብ ላይ እያደረሰ ባለው ልክ ያለፈ በደልና ግፍ በመማረር መሆኑን ገልጸውለታል:: በማያያዝም ተማሪዎቹ ህዝባዊ አመጹን ሲቀሰቅሱ የከተማዋን ነዋሪ ህብረተሰብ ሳያስታውቁ ብቻቸውን በመሆኑ ፖሊሶች በቀላሉ ሊያፍኑአቸው መቻላቸውን፣ የአመጹን መጀመር ህዝቡ እንዲያውቅ ቢያደርጉ ኑሮ ግን ህዝቡ አብሩአቸው ይወጣ እንደነበር በመግለጽ አሁንም ህዝባዊ አመጹ ተጀመረ እንጂ አላበቃም፣ በተጠናከረና በተቀናጀ መልኩ የተጠናከረ ትግል የምንቀጥልበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም ብለዋል::

## ሃይለማሪም ደሳለኝ በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ጋር የተካሄደው የልማት ውይይት ውጤታማ ነበር በማለት ቅጥፈት የተሞላበት መግለጫ መስጠቱ ተዘገበ

የብሄር ብሄረሰብ ስብጥር ያለበት የሥልጣን ክፍፍል በአገሪቱ ያለ ለማስመሰል የምክትል ጠቅላይ ሚንስቴርነትና የውጪ ጉዳይ ምንስቴርነት ሹመት ደራርቦ የተሰጠው ሃይለማሪያም ደሳለኝ ከትናንትና በስቲያ ሃሙስ በጽ|ቤቱ ውስጥ ለተጋበዙ የአገዛዙ ጋዜጤኞች በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ በሰሜን አሜሪካና አውሮፓ የተካሄደው ስብሰባ የታለመለትን ውጤት ያስገኘ ነው በማለት ከአለቆቹ በቀሰመው ቅጥፈት ህዝብ ለማደናገር መሞከሩን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከው ሪፖርት አስታወቀ።

በፈረንጆች አቆጣጠር አፕሪል 2 እና 3 በተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶች በተደረጉት የወያኔ ስብሰባዎች ብዛት ያላቸው ኢትዮጵያዊያን ከስብሰባው አዳራሽ ውስጥ እና ውጪ በመገኘት የልዑካን ቡድኑን በተቃውሞ እንዳሸማቀቁ የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮን ጨምሮ የተለያዩ ሚዲያዎች በወቅቱ በተከታታይ ዘግበውት እንደነበረ እየታወቀ፤ መለስ ዜናዊ በራሱ አምሳል እያቀረጸ የሚመድባቸው አድርባይ ሹመኞች ግን ያለምንም ሃፍረትና መሸማቀቅ ህዝቡን በእንዲህ አይነት ውሸት ለማደናገር ሲሞክሩ ለህዝቡ ያላቸውን ንቀት ብቻ ሳይሆን ሰዎቹ ለራሳቸው ስብዕና ያላቸው ክብር ምን ያህል እንደወረደ የሚያሳይ ነው በማለት ጋዜጣዊ መግለጫውን የተከታተለ ስሙ እንዳይገለጽ የፈለገ አንድ አገር ወዳድ ለሪፖርተራችን አስተያየቱን ሰጥቶአል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## መከፋፈል በቃ!

በንድፈ ሃሳብ ደረጃ የመተባበርን አስፈላጊነትና ጠቀሜታን ማንም አይስተውም። ስለትብብር በየቦታው ሲሰበክ እንሰማለን። ችግሩ ያለው ከንግግር ባለፈ በተግባር መተባበር መቻል ላይ ነው። በተለይም በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ዘላቂና ፍሬዓማ የሆነ ትብብር መፍጠር ትዕግሥትና ጥበብን የሚጠይቅ ተግባር ነው።

የምር ለመተባበር:-

- የጋራ ችግር፣ የጋራ አጀንዳ፣ ወይም የጋራ ህልም መኖሩን ማመን፣
- ስለራስ ብቻ ሳይሆን ስለሌላኛው ወገን ጥቅም መጨነቅን፤
- ነገሮችን በራስ ብቻ ሳይሆን ከሌላኛው ድርጅት እምነት አንፃር ጭምር መመልከትን፤
- ከድርጅታዊ ጥቅም በላይ ለሆኑ የጋራ እሴቶች ቅድሚያ መስጠትን፤
- የትብብርን መጠን ደረጃ በደረጃ ማሳደግን፤
- በድርጅቶች መሪዎች መካከል ብቻ ሳይሆን በአባላትና ደጋፊዎች መካከልም የእርስ
- በእርስ መተማመን መፍጠርና ማጎልበትን፤
- ለትብብር መዋቅራዊ መሠረት መስጠትን፤
- በጋራ ፕሮጀክቶች ላይ ተጋግዞ መሥራትን፤
- የመተባበር ባህልን ማዳበርን፤ እና
- አጠቃላይ በሆኑ ነቢቦች ላይ ብቻ ሳይሆን በዝርዝር የአሰራር ሂደቶችም ላይ መስማማትን ይጠይቃል።

ይህን አሟልቶ መገኘት "እንተባበር" እያሉ እንደ መስበክ ቀላል አይደለም። ይህ ሥራ ቀላል ስላልሆነም ነው እስከዛሬ ድረስ ጠንካራ የሆኑ ኅብረቶችን መፍጠር ያልቻልነው። አሁን ግን በኢትዮጵያ ፓለቲካ ውስጥ ተስፋ ሰጪ ሁኔታዎች እየታዩ ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በሰሜን አሜሪካ አትላንታ ከተማ ውስጥ ሚያዝያ 15 ቀን 2003 ዓም የጠራው ህዝባዊ ስብሰባ የኢትዮጵያ ፓለቲካ ወደ አንድ ከፍተኛ እርከን የተሸጋገረ መሆኑን በተግባር የታየበት ሆኗል።

በዚህ ህዝባዊ ስብሰባ ላይ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ተወካይ እና የኦጋዴን ብሄራዊ ነፃ አውጪ ግንባር (ኦብነግ) በመወከል ደግሞ በአትላንታ የኦጋዴን ኮሚኒቲ ተወካይ ተገኝተው ድርጅቶቻቸውን በመወከል ንግግር አድርገዋል፤ ከተሰብሳቢዎች ለቀረበላቸው ጥያቄዎችም ምላሽ ሰጥተዋል። በተወካዮቹ ንግግር እና ለጥያቄዎችም በሰጡት ምላሽ በአዳራሹ ውስጥ የነበረውን ብቻ ሳይሆን ስብሰባውን በተለያዩ መንገዶች ሲከታተል የነበረዉን አብዛኛውን ኢትዮጵያዊ አርክቷል። ስብሰባው ሁላችንም ፍትህና እኩልነት የሰፈነባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እንደምንፈልግ በማያሻማ ሁኔታ አረጋግጦልናል። ይህ በኢትዮጵያ ፓለቲካ ውስጥ ትልቅ እመርታ ነው። ኦነግና ኦብነግ ለተባበረ ትግል ያሳዩትን ቆራጥነት እናደንቃለን። በዚህ ቀጥሎ ደግሞ ኅብረታችን በጠንካራ አለት ላይ ለመገንባት መወሰድ ወደሚኖርባቸው እርምጃዎች ፊታችንን አዙረን በእርስ በእርስ መናቆር ያሳዘነውን ወገናችንን እንክሳለን ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

ለብዙ ዓመታት የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ከፍተኛው የስጋት ምንጭ የኢትዮጵያዊያን ፓለቲካ ድርጅቶች በአንድነት መቆም እንደሆነ ይታወቃል። በዚህም ምክንያት ሁሌም በኅብረት ለመቆም በምናደርገው ጥረት ላይ ሰፊ የፕሮ ፖጋንዳ ዘመቻ እንደሚከፍት በእርግጠኝነት መጠበቅ ያስፈልጋል።

በሌላ በኩል ደግሞ በቆዩ የእርስ በእርስ ቁርሾዎች እና በኢትዮጵያዊያን መካከል ያለው መተማመን ክፉኛ በመሸርሸሩ ምክንያት ይህን የኅብረት እርምጃ በጥርጣሬ የሚመለከቱ ወገኖች ከሁሉም ድርጅቶች ወገን እንደሚኖሩ መጠበቅም ይኖርብናል። የእነዚህ ወገኖቻችን ስጋት የሚቀረፈው እኛ ይበልጥ ተቀራርበን ውጤታማ ሥራ ስንከውን እንደሆነ ለአፍታም መዘንጋት የለብንም።

ሚያዝያ 15 ቀን 2003 ዓም በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ አንድ ትልቅ የማጥቃት እርምጃ የወሰድንበት ቀን ነው። በአንድነት "ኢትዮጵያዊያን በዘር አንጣላም!" ብለነዋል። ይህ ብቻ አይደለም፤ "አንተን አስወግደን እኛ በፍቅር እንኖራለን!" ብለነዋል።

በእርግጥም አዳራሹ ውስጥ እንዳደረግነው ሁሉ በተግባር እጅ ለእጅ ተያይዘን የመለስ ዜናዊን አገዛዝ እናስወግዳለን፤ በምትኩም ለሁላችንም የምትመች ፍትህና እኩልነት የሰፈነባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እንገነባለን።

**ኢትዮጵያዊያን በአንድነት "የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በቃ!" "ዘረኝነት በቃ!" "መከፋፈል በቃ!" ብለናል።**

**በቃ!!! ጋዬ!!! ይአከል!!! አሎኒ!!! ዲታህ!!! ወጣንደም!!! በስ!!! ጉደስ!!!**

---

### ህወሃት በራሱ እና በአምሳሉ በፈጠራቸው . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በገቢዎችና ጉምሩክ፣ እንዲሁም በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ በሚሰሩ የፌዴራል መንግሥትና ክልላዊ ተቋማት ውስጥ የህወሃትና የብአዴን ሰዎች ቁጥር አንድ እና ቁጥር ሁለት ሙሰኞች መሆናቸውን ጥናቱ እንዳመላከተ የተናገሩት የኢሳት ምንጮች፣ የኦህዴድ ሰዎች ደግሞ በፌዴራልና በክልላቸው በመሬት አስተዳደር ጉዳይ ላይ ቁጥር አንድ ሙሰኛ መሆናቸው ተረጋግጧል ማለታቸው ተዘግቦአል፡፡

የወያኔው ኢህአዴግ ጥናቱን ቀደም ብሎ የአከናወነና ሁኔታውን በቅጡ የተረዳ ቢመስልም በሙሥና የአንበሳውን ድርሻ የያዙትን በዋናነት የህወሃት፣ ቀጥሎ የብአዴን ከፍተኛ ባለሥልጣናት ላይ ምንም ዓይነት እርምጃ ሳይወስድ በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ የመካከለኛ ደረጃ እና አነስተኛ ባለሥልጣናት ላይ ብቻ የማስተካከል እርምጃ በመውሰድ ከ120 በላይ የኦህዴድ ባለሥልጣናትና ኃላፊዎችን ቀደም ብሎ ማሰሩ ፖለቲካዊ ጨዋታ ነው በማለት መረጃውን ያቀበሉትን የኢህአዴግ አባላት በመጥቀስ ኢሳት ዘግቦአል፡፡

እንደ ዜና ዘገባው ከህወሀት ሰዎች መካከል የዘረኛና አምባገነኑ አገዛዝ ቁንጮ መለስ ዜናዊ ባለቤት የሆነችውና የሙስና እናት በመባል የምትታወቀው አዜብ መስፍን ቁጥር አንድ በሙስና የተዘፈቀች ሰው ስትሆን፣ አዜብ ባሁኑ ሰአት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ወ/ሮ ዘርፈሽዋል በሚል ስም መጠራት መጀመሩአ ዜናው አክሎ አመልክቶአል።

አዜብ መስፍን ወይም ወሮ ዘርፈሽዋአል ከጫት ጀምሮ እንጀራ ወደ ውጭ በመላክ ባሉት ስራዎች ላይ ሁሉ ተሰማርታ የምትገኝ ሲሆን፣ በብዙ መቶ ቢሊዮኖች የሚጠጋ ሀብት ያለውን የህወሀት ኩባንያ የሆነውን ኢፈርትንም በበላይነት ታስተዳድራለች። በቅርቡ ኤቢሲ የተባለው የስፔን ጋዜጣ የሙስና እናት አዜብ መስፍን ወደ አርባ ቢሊዮን ከሚጠጋው የዘረኛው አምባገነን ባሏ መለስ ዜናዊ ተቀማጭ ሀብት ውስጥ እንደልቡአ በማውጣት በአውሮፓ እና በአሜሪካ ውድ ልብሶችንና ጌጣጌጦችን እንደሚትገዛ ማጋለጡም አይዘነጋም።

ወ/ሮ ዘርፈሽዋል ወይንም አዜብ መስፍን እኔ ከኢትዮጵያ ህዝብ ገንዘብ አልዘርፍም በማለት በተደጋጋሚ ስታስተባብል ብትቆይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ይህን የዝርፊያ ወንጀል መደበቅ ከማትችልበት ደረጃ ላይ መድረሱአን አብዛኞች የሚስማሙበት ጉዳይ ሲሆን በቅርቡ የበአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙ ነዋሪዎች ባቀረቡት ተቃውሞና በኦህዴድ ውስጥ በተፈጠረ የስልጣን ክፍፍል መነሻነት በርካታ ሰዎች በሙስና የተያዙ ቢሆንም በመሬት ሽያጩ ቁልፍ ተዋናይ የሆነችው አዜብ መስፍን መሆኗ መዘገቡ ይታወሳል፡፡

### ግንቦት7 በአትላንታ የጠራው ህዝባዊ ስብሰባ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የኦነግ ተወካይም በበኩላቸው የወያኔ አገዛዝ ላለፉት 20 አመታት በአገሪቱ ህዝብ ላይ ፈጽሟአቸዋል ያሉትን ሰቆቃዎች አንድ በአንድ ከዘረዘሩ በኋላ ህዝቡን በዘርና በሃይማኖት በመከፋፈል ቀደም ሲል የነበሩት መንግሥታት አደረሱ ከሚባሉት ጭቆናዎች ሁሉ የከፋ ወንጀል በአገራችንና በህዝባችን ላይ በመፈጸም ላይ ያለውን ይህንን አገዛዝ በጋራ ትግል አስወግደን ፍትህ የሰፈነበት አስተዳደር ማስፈን እስከቻልን ድረስ መገንጠል የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ግብ መሆን አይችልም ብለዋል።

የግንቦት 7 ሊቀመንበር በበኩላቸው ወያኔ የህዝባችንን የለውጥ ፍላጎት አቅጣጫ ለማስለወጥ ላለፉት 20 አመታት በመለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ አዕምሮ ውስጥ ፍጽሞ ያልነበረ አዲስ የልማት አጀንዳ በመፈብረክ፤ "የአባይ ወንዝን እንገድብላችኋለንና ገንዘብ አዋጡ ቦንድ ግዙ በማለት ህዝባችንን ለማደናገር ላይ ታች በማለት ላይ ይገኛል ካሉ በኋላ የወያኔ መሪዎች አባይን የመሰለ ብሄራዊ መግባባትን የሚጠይቅ ትልቅ የልማት ፕሮጄክት ለመስራት ቀርቶ በደርግ ጊዜ በስንት ልፋት ተሰርተው የነበሩትን ጣና በለስንና የአልወሮን መስኖ ልማት ያፈረሰ ቡድን መሆኑን እስከነመረጃው አቅርበዋል።

### የወያኔ አገዛዝ የስቴት ዲፓርትመንት በቅርቡ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የፓርቲ ስርአት ብቻ መሆኑን፣ እንዲሁም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጂቶች ላይ የኢትዮጵያው ዘረኛ አገዛዝ የወሰዳቸው የእገዳ ርምጃዎች አሉታዊ መሆናቸውን መግለጹ ይታወሳል፡፡

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ከሰባዊ መብት ተሟጋቾች በተደጋጋሚ የሚቀርቡበትን የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ሪፖርቶች መሰረተ ቢስና ገለባዎች በሚሉ ቃላት በማጀብ እስከ ቅርብ ጊዜ ሲያጣጥል እንደቆየ በስፋት የሚታወቅ ሲሆን በቅርብ ለተመሰረተበት ውንጀላ አገዛዙ የኢትዮጵያን የእድገት ግስጋሴ የሚያጨልም ነው በማለት ጭራሹኑ ምንም አስተያየት የለኝም ማለቱን ቮይስ ኦፍ አሜሪካ ዘግቧል፡፡

መለስ ዜናዊ በብርሃኔ ገብረክርስቶች ታኮነት የውጪ ጉዳይ ሚንስቴር አድርጎ የሾመው ሃይለማሪያም ደሳለኝ ልክ እንደ ጌታው መለስ ዜናዊ ሥልጣኔ የሌለው እና ምንም አይነት የአለም አቀፍ ግንኙነት ሥርዓትን ባልተከተለ ስድ ቋንቋ ሪፖርቱን ያጣጣለ ከመሆኑም በላይ ርባና የለሽና ትርጉም አልባ ለሆነው የስተት ዲፓርትመንት ሪፖርት ምንም አይነት አስተያየት አይኖረንም ብሏል። ሃይለማሪያም በዚሁ ዲስኩሩ የስተት ዲፓርትመንት ላቀረበው ሪፖርት ቦታ የማንሰጥ ቢሆንም ከአሜሪካን ጋር ያለን ቁልፍ ግንኙነት ግን ይቀጥላል በማለት ከአሜሪካን ሃገር የሚገኘው ደጎስ ያለ የገንዘብ ርዳታም እንዳይቋረጥ መለማመጥ የታጀበበት ንግግር ማድረጉም ታውቋል፡፡

አሜሪካ ለዘረኛውና አፋኙ የወያኔ አገዛዝ በየ አመቱ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ እገዛ እንደምታደርግ ይታወቃል፡፡

# የዴሞክራሲ ትግሉ በኢትዮጵያ: የማጥቃት ስልቶቻችን

## ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በአትላንታ በተካሄደ ህዝባዊ ስብሰባ ያደረጉት ንግግር አፕሪል 23 2011 (ክፍል 1)

### 1. መግቢያ

ከዚህ በፊት በሂውስተን ከዚያም በኖርዌይ ባደረግኳቸው ንግግሮች ከሰሜን አፍሪቃና መካከለኛው ምሥራቅ አብዮቶች ልንማራቸው ስለሚገቡ ኣራት ነገሮች አንስቼ ነበር። በነኛ ንግግሮቼ ያነሳኋቸው ነጥቦች በአጭሩ የሚከተሉት ነበሩ።

1. የነፃነትና የዲሞክራሲ ፍላጎት ለተወሰኑ ዘሮች፣ ባህሎችና ሃይማኖቶች የተሰጡ ሳይሆኑ የሰው ልጆች ሁሉ የሚፈልጓቸው እሴቶች መሆናቸውን
2. የሰሜን አፍሪቃ አብዮቶች አፍሪቃዊያን በራሳቸው ያላቸውን መተማመን በከፍተኛ ደረጃ ያዳበሩበት ክስተት መሆኑን።
3. ይህ ወቅት አፍሪቃዉያን የአገራቸውና የገዛ ህይወታቸው ባለቤት የሆኑበት ወቅት መሆኑን።

በመጨረሻም:

1. የአምባገነኖችን ባህርይ በሚመለከት በተለይ ከሊቢያና ከየመን የቀሰምናቸውን ትምህርቶች በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ነበር ።

የሰሜን ኣፍሪካና የመካከለኛው ምስራቅ ኣብዮቶች ግን ኣብዮቶቹ ከሚካሄድባቸው ኣገራት ውጭ ባሉ ኣምባገነን ስርኣት በሰፈነባቸው ኣገራት ያሉ መንግስታት ይህ ኣብዮት እነሱ ዘንድ እንዳይመጣ ለመከላከል በሚል የሚወስዷቸው ገሚስ ኣስቂኝ ገሚስ ኣሳዛኝ እርምጃዎችም ብዙ ትምህርቶችን እየሰጡን ነው:: ሁሉም ኣምባገነኖች ማለት ይቻላል የመጀመሪያ መልሳቸው "ይህ በፍጹም እኛጋ ኣይደርስም" የሚል ነው:: "እኛ የተለየን ነን:: እኛጋ ሙስና የለም፤ መልካም ኣስተዳደር ኣለ: ህዝቡ ይወደናል... ወዘተ":: እንደ መሪው ኣይን ኣውጣነት "በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ነው ስልጣናችን ላይ ያለነው: ኮንትራታችንን ሳንጨርስ የትም ኣንሄድም" የሚሉም ኣሉ:: ደጋፊዎቻችን የሚሏቸውን በገንዘብ ከሚገዟቸው ጋር ቀላቅለው የድጋፍ ሰልፍ ያስወጣሉ:: ይህ ግን ብዙ የማያዋጣ ከመሰላቸውና ትንሽ ገንዘብ ያላቸው ከሆኑ ህዝቡን ለመደለል ለኑሮ መደጎሚያ እያሉ እንደ ሳኡዲ ኣረቢያ ገንዘብ ይበትናሉ:: ገንዘቡ የሌላቸው ደግሞ በገንዘብ ፈንታ ኣስፈላጊ የሚባሉ ሸቀጦችን ነጋዴዎችን ኣስገድደው ለህዝቡ በርካሽ ዋጋ ለማቅረብ ይሞክራሉ እሱም ለረጅም ጊዜ የማያስኬድ ሲሆን የወደፊት እድገት ተስፋ ለመመገብ ይሞክራሉ:: ሁሉም በጣም የተረጋጋ ስርኣት እንዳላቸው ለሚሰማቸው ሁሉ ከመንገር ወደኋላ ኣይሉም:: የሶሪያው ኣሳድ እና ወሬ ኣቀባዮቹ (የምእራብ ኣገራት ኤክስፐርቶችን ጨምሮ) በሶርያ ስላለው ከፍተኛ መረጋጋት ኣውርተው ሳይጨርሱ በዱማ: በጃብላና እንዲሁም በደማስቆስ በሺዎች የሚቆጠሩ ነጻነት ፈላጊዎች በኣደባባይ ወጥተው ኣሳፈሩዋቸው:: ሁሉም ጉልበትንና ማባበልን እያፈራረቁ ለመጠቀም ይሞክራሉ:: የማባበያ ገንዘብ ባደሉበት እጃቸው: ጅራፍ መዝዘው ህዝቡን ይገርፋሉ:: በትንንሽ ማንኪያ የሚበትኑትን የማባበያ ስኳር ኣልልስም ያለውን በገፍ ከማሰር ኣልፈው በኣጸያፊ ሰቆቃ ቅስሙን ለመስበር ይሞክራሉ:: ከዚህ ሁሉ ጋር በማጣመር ደግሞ የበሬ ወለደ ውሸታቸውን ህዝቡ ጆሮውን እስከሚያመው ድረስ ለብቻቸው ያለጠያቂ በሚቆጣጠሩት የመገናኛ ብዙሃን ይለቁበታል:: ሌላ ቢቀር መስማት ሲሰለቸው ውሸቱን እውነት ነው ብሎ ይቀበላል ከሚል ፈሊጥ በመነሳት::

ይህንን በኣምባገነኖች ጎራ ያለ ትርምስ በጥሞና የሚመረምሩ ተንታኞች ያገኙት ኣዲስ የጊዜ ማሳለፊያ "የነገው ኣመጽ ባለተራ ማን ነው?" የሚል መላምትና ትንቢት መሰንዘር ሆኖኣል:: ይህ ግን በሙያተኞች ኣካባቢ ብቻ ሳይሆን በየኣገሩ የሚኖር የነጻነት ጥማተኛም ጊዜ ማሳለፊያ ከሆነ ሰንብቶኣል:: ለዚህ ይመስለኛል የሊቢያ፤ ሶርያና፤ የመን ወሬ ከማንቼስተርና ከኣርሴናል ግጥሚያ በላቀ የነኝህን ኣገሮች ወጣቶች: ብሎም ጎልማሶች ቀልብ የሳበው:: መቼም እንዲህ ኣይነት የትንቢት ስራ ለባለሙያዎችም እንዴት ከባድ እንደሆነ ይታወቃል:: ስለዚህም ከውጤቱ ይልቅ ወደትንቢቱ ለመሄድ የሚቀርበው ትንተና የበለጠ ትኩረት ይሰጠዋል:: ትንተናዎቹ ደግሞ በሁለት ሰፋፊ ጉዳዮች ዙሪያ ያጠነጥናሉ::

እነኝህም:

1ኛ: ለውጥ ለመፍጠር ኣስፈላጊ የሆኑ ነባራዊ ጥልቅ መዋቅራዊ ምክንያቶች (deep objective structural factors) መኖር ኣለመኖር ላይ ያተኮሩ ጉዳዮች ናቸው:: እነኝህ ዋና ዋና ምክንያቶች የታወቁ ናቸው:: ቅጥ ያጣ ድህነት፤ መያዢያ የጠፋው የዋጋ ግሽበት፤ ብልሹ ኣስተዳደር፤ ሙስና፤ የፍትህ እጦትና ባጠቃላይ ኢዴሞክራሲያዊ ኣስተዳደር ናቸው:: በነኝህ መስፈርቶች ከተጠቀምን በኣፍሪካ ብቻ ለለውጥ የተዘጋጁ በጣም ብዙ ኣገሮች ኣሉ:: ከሰሀራ በታች ካሉት 48 ኣገሮች ውስጥ ኢትዮጵያን ጨምሮ 39ኙ ህዝቡ በቂ ነጻነት የማያገኝበት ወይም በፍጹም ነጻነት የሌለበት የድህነት ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ነው የሚኖረው::[1] ሌሎች ኣካባቢዎችን ስሌት ውስጥ ካስገባን ለለውጥ የተዘጋጁ ኣገሮችን ቁጥር የትየለሌ ያደርገዋል:: ስለዚህ በዚህ ምክንያት ላይ ከተመረኮዝን መጪውን ለውጥ በተመለከተ ያሉትን ተረኞች ኣንድ ሁለት ብሎ ለመተንበይ ያስቸግራል::

2ኛ: እነኝህ ጥልቅ መዋቅራዊ ምክንያቶች መኖራቸው ብቻውን ግን ለውጥ ወዲያውኑ ያስነሳል ማለት ኣይደለም:: በኣንድ ወቅት በገዢዎች ውስጥም ሆነ በተገዢዎች ውስጥ የሚገኘው የስነልቦ ሁኔታና ከዚህም ጋር በተያያዘ የሚወስዷቸው የተለያዩ እርምጃዎች በዚያ ተጨባጭ ሁኔታ ለውጥ በምን ፍጥነት ሊመጣ ይችላል የሚለውን ይወስናል:: በተለይ ለዴሞክራሲ የሚታገሉ ሀይሎች "በመዳረሻው ቦታ" (end game) ላይ የተስማማና ወጥ ኣመለካከት መኖር ለውጡን በቶሎ በማምጣት ላይ ኣስፈላጊነቱ ኣጠያያቂ ኣይደለም:: ስለዚህም ማን ይከተላል የሚለውን ለመተንበይ ሁለተኛው ምክንያት ላይ የበለጠ ማተኮር ይበጃል::

ይህ ግን ቀላል ስራ ኣይደለም:: ኣምባገነን ስርኣቶች ሲወድቁ እንደ ቅል ባዶ መሆናቸው የሚጋለጠውን ያክል በስልጣን ላይ ሳሉ ማህበረሰቡን ፍርሀት መቀመቅ ውስጥ ከትተው ስለሚያኖሩት ህብረተሰቡ በዚያ ስርኣት ላይ ያለውን ስሜት ለማወቅ ኣይቻልም:: እንኳን ያንን ሰርኣት ለመጣል ይነሳ ኣይነሳ ለመተንበይ:: ለምሳሌ የሶቭየት ህብረት ለመፈራረስ ስድስት ወራት ሲቀረው ኣንድ ምዕራባዊ የህዝብ ኣስተያየት ሰብሳቢ ድርጅት ሩሲያ ድረስ ሄዶ ባደረገው ጥናት ከህብረተሰቡ 88% የሚሆነው የኮሙኒስት ፓርቲውንና የኮሙኒስት ስርኣቱን በጽኑ እንደሚደግፍ ነበር ያስታወቀው:: ከላይ እንደጠቀስኩትም ሁሉም ስርኣቶች ምን ኣረመኔ ቢሆኑ ህሊናቸውን ለሆዳቸው የሸጡ (በተለይም ያንን ስርኣት በመጠቀም ንብረት የሰበሰቡ ወይንም ለመሰብሰብ የሚያልሙ) ደካማ ደጋፊዎች ኣያጡም:: እነኝህን ጥቂት ደጋፊዎች ባላቸው የመገናኛ ብዙሀን በመጠቀም ብዙ ለማስመሰል ስለሚሞክሩም የዋሁን ተመልካች ሊያሳስቱ ይችላሉ:: በቅርቡ በሶሪያ ላይ እንደተሳሳቱት ብዙ ባለሙያዎች ማለት ነው:: በመያዚያ 29 1997 የመለስ ሰልፍ እንዳየነው እንደ ኢትዮጵያ ባለ ድሀ ኣገር በ30 ብር ክፍያም ብዙ ሰው ማሰለፍ ይቻላል በነጋታው የምር ስሜቱን ለማሳየት የተቃዋሚውን ሰልፍ በነጻ ቢቀላቀሉም:: ስለዚህ ተመልካቾች በኣንድ ኣብዮታዊ ወቅት በኣምባገነን መንግስቶች እንቅስቃሴዎች ኣካባቢና ለነኝህም እንቅስቃሴዎች በህዝቡ ዘንድ የሚንጸባረቁ ስሜቶችንና መልሶችን በኣትኩሮት በመመልከት ሁኔታው ለለውጥ የበሰለ መሆን ኣለመሆኑ ላይ "ትንተናዊ" ግምት ይሰጣሉ:: በተለይም በመንግሥት ኣካባቢ የሚታዩ የተለዩ መቅበጥበጦች: በህዝቡ ወገን ደግሞ ከወትሮው የተለየ የመዳፈር ስሜቶች ወይንም የመተባበር ምልክቶች ሁኔታዎች ከቁጥጥር ውጪ እየሄዱ መሆናቸውን የሚያመለክቱ ክስተቶች ተደርገው ይወሰዳሉ:: እኔም ከዚህ በታች ለውይይት መተንኮሻ እንዲሆን የሰሜን ኣፍሪካው ኣብዮት ከተጀመረ ጀምሮ የመለስ ኣገዛዝ የሚወስዳቸውን የተለያዩ እርምጃዎችና ማህበረሰቡም ለነኝህ እርምጃዎች የሚሰጠውን ምላሽ በመመርኮዝ የሚቀጥለው የለውጥ ተረኛ መለስ ሊሆን ይችል ይሆን ወይ? በሚለው ጥያቄ ላይ ያለኝን ትንተናዊ ግምት እሰጣለሁ:: ከዚያም ይህ ለውጥ ከተጀመረ ስኬታማ እንዲሆን በጣም ኣስፈላጊ የሆነውን የመዳረሻ ስምምነት በሚመለከት ኣንዳንድ ኣስተያየቶችን ሰንዝሬ ኣጠቃልላለሁ::

### 2. የሰሞኑ የነመለስ እንቅስቃሴዎች ያሳዩዋቸው ምልክቶች

መቼም ማንም የኢትዮጵያን ሁኔታ በቅርብ የሚከታተል ሰው ልብ እንደሚለው መለስና ቡድኑ ካለፉት ሁለት ወራት ግድም ጀምሮ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ከወትሮው ለየት ያለና ጭንቀት የወለደው እንደሚመስል መካድ ኣይቻልም:: ለወትሮው ነገሮችን በብልጠት ማለፍ የሚችለው ኣውራቸው በየሳምንቱ የተገለባበጠ መልስ ሲሰጥ: ከሳምንት በፊት ያለውን ፍጹም የረሳ ብቻ ሳይሆን ክፉኛ የተጨነቀ ኣእምሮ የወለደው መደናበርና ድንፋታ መሆኑን ሊስተው ኣይችልም:: ኣተኩረን መመልከት ያለብን እርሱ የተናገረውን ብቻ ሳይሆን እሱን ተከትሎ ትንንሾቹ ካድሬዎች በሹክሹክታ ለወሬ ኣናፋሾቹ የሚነግሩትንና በህዝቡ ዘንድ እንዲስፋፋ የሚያደርጉትን ወሬም ጭምር ነው::

በመጀመሪያ ሁላችንም የሰማነው ሁሉም ኣምባገነኖች እንደ በቀቀን የሚደጋግሙትን "ይህ ችግር እኛጋ ኣይደርስም" የሚለውን፤ እውነትን ላለማየት ኣውቆ የታወረ ሰው የሚሰጠውን መልስ (ፈረንጆች denial የሚሉት) ነበር:: መለስ ኣይኑን በጨው ኣጥቦ እኛ ዴሞክራሲያዊ ስርኣት ነው ያለን: ህዝብ የሰጠንን ኮንትራት ሳንጨርስ የትም ኣንሄድም የሚል የራሱን ሰዎች ለማረጋጋት የተሰጠ መልስ ነበር:: ይህ ግን ከሀሰትነቱ በተጨማሪ በተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት ያስፈልጋሉ ከሚባሉት መስፈርቶች ኣኳያ ሲታይ ውሀ የሚቋጥር መልስ ኣልሆነም:: ስለዚህ በመጀመሪያ የተመረጠው ስለዚህ ነገር ጭራሹኑ ኣለማውራት ነበር:: የሊቢያው ኣብዮት እስከሚጀመር ድረስ በረከት የሚቆጣጠራቸው መገናኛ ብዙሀን ምንም ነገር ኣያወሩም ነበር:: ከውጭ የሚተላለፉ የሚዲያ ተቋማትም (የኣሜሪካ ድምጽ: የጀርመን ድምጽ: ኢሳት: ኣልጀዚራ ወዘተ) ከዚህ በፊት ከነበረውም በላይ ኣገር ውስጥ እንዳይሰሙ በሞገድ ተመቱ:: ጋዳፊ ህዝቡን በኣውሮፕላን መደብደብ ሲጀምር ራሳቸው ወሬውን በሰፊው ማናፈስ ጀመሩ:: መልእክቱ እኛም እንደዚህ ነው የምናደርገው ብለው ሽብር ለመንዛት ነበር:: ጋዳፊ በተራው በምእራባውያን በኣውሮፕላን መደብደብ ሲጀምርና መውደቁ ኣይቀሬ መሆኑ ሲታይ: ህዝቡም ቀልቡን በሙሉ እዚሁ የነጻነት እንቅስቃሴ ላይ ማድረጉን ሲረዱ እሱንም ትተው የማህበረሰቡን ትኩረት በፍጹም የሚያስቀይሱበት መንገድ ማሰላሰል ውስጥ ገቡ::

ይህ ኣቅጣጫ የማስቀየር ኣካሄድ መቼም ተክነንበታል ብለው የሚያምኑበት ስልታቸው ነው:: እንደምታስታውሱት እነሱ ብር በማተም የፈጠሩት የዋጋ ግሽበት ማህበረሰቡን ኣስመርሮ ኣመጽ ውስጥ ሊከተው ነው ብለው ሲፈሩ ያላግባብ ዋጋ የሚጨምሩ ነጋዴዎችን እናስራለን ብለው በ 17 እቃዎች ላይ የዋጋ ገደብ ኣስቀመጡ:: ለሁለት ሳምንታት የህዝቡን ቀልብ ለመሳብ ቢችሉም እቃዎቹ ባጠቃላይ ከገበያ ሲጠፉ የነበረው ችግር ተባብሶ መቀጠሉ ይታወቃል:: ለነመለስ ግን ቀድሞውንም ችግሩን ለመፍታት ሳይሆን ኣቅጣጫ ማስቀየስ ስለሆነ ኣላማቸው ይህንንም እንደ ጊዜያዊ ድል ሳይቆጥሩት ኣልቀረም:: ጊዜያዊ ከጭንቅ መውጫ መፍትሄዎች ችግራቸው ግን መሰረታዊ ችግሮቹን ኣለመፍታታቸው ብቻ ሳይሆን ኣንዳንዴ ችግሩን ለማባባስ መቻላቸው ነው:: ችግሮቹን ከመሰረታቸው ለመፍታት የማይችሉ ስርኣቶች ግን ሌላ ምንም ኣማራጭ የላቸውም:: እስከመውደቂያቸው ድረስ ለኣንድ ቀንም ቢሆን ከስልጣን ያቆየናል ያሉትን ጊዜያዊ ማስቀየሻ እየፈጠሩ: ቀናቸውን ይቆጥራሉ::

ደንበኛው የማስቀየሻ እንቅስቃሴ የተጀመረው ከዚህ በኋላ ነበር:: የትኛው የህዝቡን ቀልብ እንደሚይዝ ለመፈተን በተለመደው "የውጭ ሀይሎች መጡብህ" ማስፈራሪያ የተጀመረው በግብጽ ላይ ነበር:: መለስ ከመሬት ተነስቶ ለውጭ መገናኛ ብዙሀን በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ "ግብጽ መንግስቴን ለማናጋት ተቃዋሚዎችን ትረዳለች" ኣለ:: እነማንን? ቢባል መልስ የለም:: ለምን ይህን ታደርጋለች ለሚለው መልሱ ግልጽ ኣይደለም ምክንያቱም ከዚያ በፊት ብዙም ሳይቆይ ግብጽና ኢትዮጵያ ስላላቸው ወዳጅነትና ግብጾች በኢትዮጵያ ኢንቬስት ስለማድረጋቸው ነበር የሚነገረን:: መለስም በሚገርም ሁኔታ በዚሁ ቃለምልልስ "ግብጽ ኢትዮጵያን ብትወር ለወሬ ነጋሪም ሰው ኣይተርፉትም" ብሎ ደነፋ:: የኣገሬውን ህዝብ ኣቅጣጫ ለማስቀየር መሆኑ ያልገባቸው የውጭጋዜጠኞች "ሰውየውን ምን ነካው? ጦርነትን ምን ኣመጣው?" ብለው የሰውየውን ጤንነት መጠራጠር ጀመሩ::

(ክፍል 2 ሳምንት ይቀጥላል)

[1] ፍሪደም ሀውስ የ 2011 ሪፖርት

## የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ዜጎችን እያስገደደ ስለ አባይ ግድብ ግንባታ ማወያየቱን ቀጥሎበታል። ህዝቡ የዲያስፖራውን ኮሚኒቲ እንዲያወግዝም ግፍት እየተደረገ ነው

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየናረ በመጣው የኑሮ ውድነት የተማረረውን ህዝብ ትኩረት በአባይ ግድብ ግንባታ ዜና አቅጣጫ ለማሳት ቆርጦ የተነሳው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ፡ በተለያየ ክልሎች የሚገኙ የመንግሥት ሠራተኞችን ፤ ተማሪዎችን እና መምህራኖችን በግዴታ ስብስቦ ስለ 5 አመቱ የትራንስፎርሜሽን ፕላን እንዲወያዩ እያደረገ መሆኑን የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ አስታወቀ።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት በሁሉም ቦታዎች እየተካሄዱ ባሉት ስብሰባዎች ከፍተኛውን ትኩረትና አጽንዖት የተሰጠው ካለፈው ወር አጋማሽ ጀምሮ በአገሪቱ ያሉ መገናኛ ብዙሃን በሙሉ ሰፊ የዘገባ ሽፋን እንዲሰጡት የተደረገው የአባይ ግድብ ግንባታ ጉዳይ ሲሆን ህዝቡ ለግድቡ ሥራ ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ቦንድ በመግዛትና የወር ደመወዙን በመልቀቅ እንዲያዋጣ ግልጽና ተዘዋዋሪ ተጽዕኖዎች እየተደረጉበት ነው ተብሎአል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በየመሥሪያ ቤቱ አስርጎ ያስገባቸው የወያኔ ካድሬዎች እና የሥራ ሃላፊዎች፤ በተጠራው ስብሰባ ላይ ሁሉም እንዲገኝ አስቀድመው በሰጡት ጥብቅ ትዕዛዝ ምክንያት የታዘዘውን በመፈጸም የስራ ዋስትናውን ከማረጋገጥ ውጪ ምንም አማራጭ የሌለው ሁሉ ለመገኘት እንደተገደደ ታውቋል። በአገሪቱ ውስጥ በየዕለቱ እየናረ በመሄድ ላይ ባለው የገቢያ ዋጋ ምክንያት የወር ደመዎዝ አንድን ቤተሰብ በአግባቡ ማስተዳደር ተስኖት ልጆች ባዶ ሆዳቸውን ትምህርት ቤት እየሄዱ ክፍል ውስጥ በረሃብ ተጥወልዉለው እንደሚወድቁ በተደጋጋሚ በሚዘገብበት አገር ፤ በአፈጮሌ ካድሬዎች እና የስር ዓቱ አሽቃባጮች ግፊት እያንዳንዱ የመንግሥት ሰራተኛ የታዘዘውን የወር ደመወዝ ለመልቀቅ እየተገደደ ነው። የኢትዮጵያ ቴሌቪዝን ላይ ቀርበው ለግንባታ በፈቃዳቸው የወር ደመዎዛቸውን መልቀቃቸውን የድምጽ ማጉያ ጨብጠው ከሚዶሰኩሩት ካደሬዎች አጠገብና በስተጀርባ የተቀመጡ የበርካታ ሰራተኞች ፊት ላይ የሚነበበው ኀስቁልና የሚመሰክረው ይህንን ሃቅ እንደሆነ ዘጋቢያችን አስተያየቱን አክሎ ዘግቧል።

ይህ በዚህ እንዳለ ባለፈው ሃሙስ ሚያዚያ 12 ቀን በመላ አዲስ አበባ የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃና የመሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአገዛዙ ባለስልጣናት ልዩ ትዕዛዝ የግማሽ ቀን የትምህርት መርሃ- ግብራቸው ታጥፎ ከአዲስ አበባ የትምህርት ቢሮ በፕላዝማ የተላከላቸውን የወያኔ መልዕክት ሲከታተሉ መዋላቸው ታውቋል።

በፕላዝማ እንዲተላለፍ ከተደረገው የአባይ ወንዝ ላይ ስለሚገነባው ሚሊኒየም ግድብ ሌላ ጸረ- ልማትና ጸረ- ሠላም አቋም በማራመድ ላይ ናቸው የተባሉት በአገር ውስጥ እና ከአገር ውጪ የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች እነማን እንደሆኑ ለተማሪዎቹ መግለጫ መሰጠቱንና እንዚህን ሃይሎች እንዲያወግዙ መጠየቁን ተያይዞ የደረሰን ዜና ያስረዳል።

### የቻያናና የህንድ ኩባንያዎች ያለጨረታ የንግድ ፈቃድ ተሰጣቸው

በሞጆ የጋራ መኖሪያ ወይም ኮንዶሚኒየም ቤቶች ሳይት አቅራቢያ የሚገኘው ”ህንሰም የመስታወት ፋብሪካ- በቻይና እና በህንድ‘ የተባለ ኩባንያ በልደታ በመገንባት ላይ የሚገኙትን በርካታ ባለ ሰባት ዘመናዊ ፎቅ የጋራ ቤቶችና የንግድ ሱቆች የመስኮትና የበር መስታወቶችን እንዲያቀርብና እንዲገጥም በዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ባለሥልጣናት ፈቃድ ያለጨረታ እንደተሰጠው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ጽ/ቤት የዜና ምንጮቹን በመጥቀስ ዘገበ፡፡

በምሥራቅ አፍሪካ ገበያ ትልቅ የመስታወት አቅራቢ ፋብሪካ ይሆናል ተብሎ በትግራዩ ገዢ ጉጂሌ ከፍተኛ ባለሥልጣናት እና በቻይናና ህንድ ሰዎች ባለቤትነት ተመስሎ የተመሠረተው ህንሰም የመስታወት ፋብሪካ ፣ የውጭውን ገበያ መቆጣጠር ባለመቻሉ የሀገር ውስጥ የልማት ድርጅቶች በሚያደርጉት ጥቃቅን ግንባታዎች ውስጥ ሳይቀር በባለሥልጣናቱ ግልጽ ትዕዛዝ ያለ ጨረታ ሥራዎችን እንዲይዝ በመደረጉ ሥራቸውን በሃገሪቱ ሕግ-ተብየ ማዕቀፍ እንዳያከናውኑና የሀገር ውስጥ አምራች ድርጅቶችም ከገበያው እኩል ተጠቃሚ እንዳይሆኑ እንዳደረጋቸው ምንጮቹ መግለጻቸውን ኢሳት አስታውቋል፡፡

እንደ ኢሳት ዘገባ የሰባተኛ ዙር የጋራ ቤቶች ዕጣ ይወጣበታል ተብሎ የሚጠበቀው የልደታ ሳይት ዘመናዊ ኮንዶሚኒየም ቤቶች ላይ በቅርቡ የመስኮት መስታወት የመግጠሙ ሥራ የሚጀምር ሲሆን የዘረኛው አገዛዝ ባለሥልጣናት፣ ሆድ አደሮች፣ የወያኔ ካድሬዎችና የመከላከያ ሠራዊት አዛዦች ሳይቀሩ እነዚህን የጋራ ቤቶች የማግኘት ፍላጎት በማሳየታቸው የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ጽ/ቤት ኃላፊዎች ወደ ዕጣ በሚገቡና በዕጣ በማይካተቱ ብሎኮችና የቤቶች ቁጥር ብዛት መጨቃጨቃቸው ታውቋል።

ይህ የአሁኑ የወያኔ ግፈኛ አገዛዝ ርምጃ በመስታውት ሽያጭ የተሰማሩት ነጋዴዎችን ሙሉ በሙሉ ከገበያ የሚያስወጣቸው በመሆኑ በዚሁ የንግድ ስራ ለረጅም ጊዜ ተሰማርቶ ለመቆየት እንደማይችሉ እየተናገሩ መሆናቸውን ዘጋቢዎቹ ሪፖርት ማድረጋቸውንም ኢሳት አክሎ ገልጿል።

በሌላም በኩል ኢሳት በማያያዝ ባወጣው ዘገባ 30 ሺህ የሚጠጉ የዘረኛው አገዛዝ ካድሬዎችና የሠራዊት አባላት የነበሩ ግለሰቦች በተለያዩ ማህበራት ተደራጅተው በፌዴራል ደረጃ የንግድ እንቅስቃሴ ለማድረግ በዝግጅት ላይ ሲሆኑ አብዛኞቹ ማህበራት በልደታ ዘመናዊ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ የሚገኙትን የንግድ ሱቆች ለማግኘት በአገዛዙ ባለሥልጣናት በኩል ጥያቄ ማቅረባቸውን ገልጿል፡፡

## “ከአባይ ግንባታ በፊት የታፈነው ህዝብ ይፈታ!!” የሚል ወረቀት በአርባምንጭ ከተማ ተበተነ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በወያኔ አፈና ሥርዓት ላይ ትዕግሥቱ መሟጠጡን በተለያየ ህዝባዊ ተቃውሞ እየገለጸ ካለው የደቡብ የአገራችን ክፍል በጋሞጎፋ ዋና ከተማ በአርባ ምንጭ ህዝቡን ለተቃውሞ የሚቀሰቅሱ ጽሁፎች መበተናቸውን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአርባ ምንጭ አስታወቀ።

በተበተኑት ወረቀቶች ላይ ከታዩት መፈክሮችና ቀስቃሽ መልዕክቶች ከፊሎቹ “ ከአባይ ግድብ በፊት የታፈነው ህዝብ ይፈታ! ከውትድርና ቅጥር በፊት በሱማሌ፤ በቡሩንድ በዳርፉር የተገደሉ ወገኖቻችን መርዶ ለዘመድ አዝማድ ይነገር! ባድሜን በህግ አሸንፈናል በማለት በሃሰት ሰላማዊ ሰልፍ እንዲንወጣ ያደረጉን ስዩም መስፍንና አጋሮቹ ለፍርድ ይቅረቡ!! በስውር የተገደሉ ሰዎች ዝርዝር ይፋ ይውጣ !! አምባገነኖች አባይን አይገድቡም!! ከግድቡ በፊት ለተራቡት ዳቦ ይሰጥ !! የሚሉ ይገኙበታል።

በአርባምንጭ የሚገኙ የወያኔ ካድሬዎችና የዞኑ አስተዳዳሪዎች እየተባባሰ የመጣውን የህዝብ ስሜት እንዴት ለማረጋጋት እንደሚቻል ለመምከር አስቸኳይ ስብሰባ ጠርተው እንደነበርና በስብሰባው ወቅት በተደረገው ውይይት ካዲሬዎች ለሁለት በመከፈል ከፊሎቹ የህዝቡን ፍላጎት እና ጥቅም ማስጠበቅ ስላልቻልን ሥራ እንልቀቅ አሊያም ለህዝብ ጥያቄ ተገቢው ምላሽ ይሰጥ እስከማለት እንደደረሱ ተያይዞ የደረሰን ዜና ያስረዳል።

ወያኔ የህዝባችንን ትኩረት ወደ አባይ ግድብ ግንባታ በማዞር በሰሜን አፍርካ የተነሳው አይነት ህዝባዊ ማዕበል በአገራችን እንዳይቀጣጠል ለማዘናጋት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የጀመረው ዘመቻ አርባምንጭን ጨምሮ በተለያየ የአገራችን ከተሞች እንዲሁም ባለፈው ቅዳሜ ሚያዚያ 1 እና 2 በሰሜን አመሪካ ሳይሳካ እንደቀረ ገሃድ ወጥቶአል።

### የሐረር ዞን የመሬት አስተዳደርና የካሳ ክፊያ ሹም . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የሃራሪን ክልል በጋራ ከሚያስተዳድሩት የኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት ኦህዲድና የሃራሪ ብሄራዊ ሊግ ባለስልጣናት ጋር የቅርብ ግንኙነት ያላቸው 2 ሰዎች አቶ ሃሺም እንዲሪስን በሙስና በመደለል ተገቢ ያልሆነ የመሬት ስምሪት ለማግኘት ሞክረው ስላልተሳካላቸው ፍጹም አረሜኔያዊ በሆነ ጭካኔ እርምጃ የግድያ ወንጀል እንደፈጸሙባቸው የገለጸው የሃራሪ ሪቫይቫል ንቅናቄ ፤ የሃራሪ ክልል ከየትኛውም ሌሎች ክልሎች የከፋ ሙስና፤ ዘረፋ ፤ የስልጣን ብልግናና ጭቆና የሚፈጸምበት ክልል መሆኑን አጋልጧል።

የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ ከስፍራው የሚገኘውን ሪፖርተሩን ዜና መሠረት በማድረግ ባቀረበው የሚያዚያ አስራ አንዱ ስርጭት፤ አቶ ሃሽም እንዲሪስ በከልሉ በተንሰራፋው ሙስናና የስልጣን ብልግና በተማረሩ ታጣቂዎች ተገደሉ ተብሎ የተላለፈው ዜና ከዚህ በላይ በተዘገበው እንዲስተካከል ስንጠይቅ ለተፈጠረው ስህተት የሟችን ቤተሰብ ፤ እንዲሁም የትግል ጓዶቻቸውን ይቅርታ እንጠይቃለን። በዚህ አጋጣሚም ቤተሰብ፤ ዘመድ አዝማድ ሁሉ መልካም መጽናናት እንዲያገኙ ልባዊ ምኞታችንን እንገልጻለን።

### ሃይለማሪም ደሳለኝ በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የሃይለማሪያም ደሳለኝን ጋዜጣዊ መግለጫ ከኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድህረ ገጽ መመልከታቸውን የገለጹ አንድ የውሃ ልማት ማህንዲስ “የአባይን ግድብ የሚያክል ትልቅ ሃብትና ብሄራዊ መግባባትን የሚጠይቅ ፕሮጄክት ሥራ ምኑም ሳይጨበጥ ገና ከጅምሩ በተለመደው ተራ የወያኔ ቅጥፈት ፕሮፖጋንዳ ጋጋት ማጀብ ፡ የፕሮጀክቱ ሃሳብ ከጥንስሡ ርካሽ የሆነ ተወዳጅነትን ለማግኘትና ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ የመጣውን ህዝባዊ ተቃውሞ አቅጣጫ ለማስለወጥ የታለመ መሆኑን ፍንትው አድርጎ ያሳያል” ብለዋል

አያይዘውም ሃይለማሪያም ደሳለኝ እና የወያኔ አለቆቹ ስኬታማ ነው የሚሉት የሰሜን አሜሪካው እና የአውሮፓው ስብሰባ ላይ ለድጋፍ ከተገኙት አብላጫው ትግሪኛ ተናጋሪ የሆኑ የወያኔ አባላት መሆናቸው እየታወቀ “ኢትዮጵያዊው እና ትውልደ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የልማት ዕቅዳችንን ደግፎታል “የህዳሴ ግድብ” ብለን የሰየምነውን የአባይ ግድብ እቅድ ለማሳካት ማንኛውንም አይነት ድጋፍ እናደርጋለን ብለዋል” የሚሉት አገር ውስጥ ያለውን ህዝብ የአገር ፍቅር ስሜት በመቆርቆር የስልጣን ዘመናቸውን ለማራዘም ከልተቻለም ደግሞ “ማምሻም እዲሜ ነው” እንዲሉ በግብጹ ሆሴን ሙባረክና በቱኒዚያው ቤን አሊ ላይ በድንገት የደረሰው አይነት መፈናቀል እንዳይደርስባቸው ጊዜ ለመግዛት መሆኑን ህዝቡ ጠንቅቆ ይረዳል ብለዋል።

በሰሜን አሜሪካ በዋሽንግተን ዲሲ ተደረጎ የነበረው ስብሰባ እንዲቋረጥ ሲደረግ ስብሰባውን የበተነው በዕለቱ ስብሰባውን በሊቀመንበርነት የሚመራ የነበረው ሌላው የመለስ ዜናዊ ጀሌ ግርማ ብሩ ሳይሆን ለሃይለማሪያም ደሳለኝ በታኮነት የተመደበው የህወሃቱ ብርሃኔ ገብረክርስቶስ እንደነበረ በወቅቱ መዘገቡ ይታወሳል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org